የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር ኦ/1162/11/831
ቀን ተሐሣስ 25 2015

ለአርጎባ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት /አህዴድ/

ሰመራ፤

ጉዳዩ፣ **የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባዔ አስመልክቶ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ ስለማሳወቅ፤**

የአርጎባ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት /አህዴድ/ ነሐሴ 25 ቀን 2014 ዓ.ም. በቁጥር አ/ህ/ዴ/ድ/22/2014 በተጻፈ ደብዳቤ ነሐሴ 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ያካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ በሚመለከት የጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት አቅርቧል፡፡

ቦርዱ ታህሣሥ 21 ቀን 2015 ዓ.ም. ባካሄደው ስብሰባ ፓርቲው ከሪፖርቱ ጋር አያይዞ ያቀረባቸውን ሰነዶች ከሕጉ፣ ከፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና የቦርዱ ታዛቢዎች ካቀረቡት ሪፖርት አንፃር መርምሮ ፓርቲው ነሐሴ 23 ቀን 2014 ዓ.ም. ያሻሻለው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ላይ ያሉ ከአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ጋር የሚቃረኑ አንቀፆች ተፈፃሚ እንዳይሆኑ ፤ እንዲሁም ጠቅላላ ጉባኤው በቀጣይ ስብሰባው አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርግባቸው ወስኗል፡፡

**በዚሁ መሠረት፡-**

ሀ) ፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ ለማሻሻል ጠቅላላ ጉባኤው ለማዕከላዊ ኮሚቴው ሙሉ ውክልና የተሰጠ መሆኑ እና በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 34.1 መሰረት መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻል ስልጣን የጠቅላላ ጉባኤው በመሆኑ ተገቢው የደንብ ማሻሻያ መደረግ ያለበት በመሆኑ፤

ለድምጽዎ የሚያምኑን

አድራሻ - ቦሌ ክፍለሚንን
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ - ገጽ
www.nebe.org.et

**ለ)** በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 21.1 ላይ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ብዛት 31 ሆኖ እያለ 39 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የተመረጡበት ሁኔታ ከመተዳደሪያ ደንቡ ጋር የማይሥማማ በመሆኑ፤

**ሐ.** በአዋጅ 1162/2011 አንቀጽ 93/2 /ሀ/ መሰረት የፓርቲዎች ግንባር መፍጠር የሚወሰነው በጠቅላላ ጉባኤ በመሆኑ፤

**መ.** የማዕከላዊ ኮሚቴ ቁጥር ራሱ ማዕከላዊ ኮሚቴው መወሰኑ ከህጉ ጋር ስለሚቃረን ፓርቲው በቀጣይ በሚያካሂደው ጠቅላላ ጉባኤ በማስወሰን የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ አድርጎ እንዲያቀርብ ቦርዱ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

በመሆኑም ቦርዱ ፓርቲው በቀጣይ በሚያካሂደው ጠቅላላ ጉባኤ ከላይ ከ **"ሀ" - "መ"** በተገለፀው መሠረት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ማሻሻያዎችን አድርጎ ሪፖርት እንዲያቀርብ እያሳወቀ ነሐሴ 23 ቀን 2014 ዓ.ም. የተካሄደውን ጠቅላላ ጉባኤ እና የተላለፉ ውሳኔዎችን የመዘገበ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር

ውብሸት አየለ ጌጤ
Woubshet Ay... Ge..e
Deputy Chairperson National ... toral Board